<u>ተውሒድ አላህ ወይስ ስላሴ?</u>

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን ወንድም እህቶቼ እንደምን ሰነበታችሁ? ረደኤተ እግዚአብሔርን እየተማጸንን የእመቤታችንን ልመናና የመላእክትን ተረዳኢነት የቅዱሳንን በረከት እየለመንን ከዚህ ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ክፍላት አንድ ቁምነገር ለማዬት እንሞክራለን። ተውሒድ አላህ ወይስ ስላሴ የተሰኘው ይህ ተከታታይ ጽሑፍ የቃሉን መሰረታዊ እስላማዊና ክርስቲያናዊ አረዳድ ከመጻሕፍቱ እያመጡ መሞገትና ትክክለኛ ትርጉሙን የሚያሳይ ሲሆን በሁለቱም ሃይማኖት ውስጥ ከቃሉ ጀርባ ያለውን አረዳድና እሳቤ ያሳያል ብለን እናስባለን። የሰዎች ሁሉ መዳን ፈቃዱ የሆነ እግዚአብሔር አዕምሯችንን አሰባስበን በማስተዋል እንድናነብና እንድንጠቀም ይርዳን መልካም ንባብ።

በዓለም ካሉ አንድ አምላክ እናመልካለን ከሚሉ ታላላቅ ሃይማኖቶች መካከል አይሁድ፣ ክርስትና እና እስልምና ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው። ምናልባት ከነዚህ ውስጥ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የሆኑት ክርስትና እና እስልምና በመሆናቸው የአይሁድን ብዙም ጠልቀን አንመለከትም። አንዳንድ ምስኪን ሙስሊም ክርስቲያኖች ስላሴ ስንል ሶስት አማልክት አድርግው ያስባሉ እንደዛም በድፍረት ይናገራሉ። ምክንያቱ ደሞ ያልገባቸው ኡስታዞቻቸው የስላሴ ምንነት አይደለም ማንነት ካልገባው ከአላህ ስለወሰዱና ያንን የተንሸዋረረ ሃሳብ ይዘው ስለሚመጡ ነው። ሙሉ የሙስሊም ኡማህ ደሞ እነዚህ ያልገባቸው ሰዎች ላይ የተንጠለጠለና በራሱ አዕምሮ የማይመራ ወንዝ በመሆኑ በተቀደደለት ቦይ አንዳችም ሳያጉረመርም መፍሰሱ አይገርመንም። አዕምሯቸውን ተጠቅመው ይህ ነገርኮ እንደዚህ አይደለም! ይሄ እንዴት እንዲህ ይሆናል? ብለው የሚጠይቁ ሙስሊም ወገኖችም የሚደርስባቸው ስድብና ዘለፋ ግፋ ሲልም ማስፈራሪያ ለጉድ ነው። እስኪ ወደጉዳያችን እንግባና መጻሕፍቱ ምን እንደሚሉ አንድ በአንድ እንይ።

በአይሁድ ስርዓተ አምልኮና እምነት ውስጥ ዛዳግም 6፡4 “እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላክህ አንድ ነው” የሚለው ጥቅስ እጅግ በጣም ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና የንግግራቸውም ሆነ የሃይማኖታቸው መጀመሪያና መሰረት ነው። የእኛ የክርስቲያኖችም እምነት ይኸው ነው። ታዲያ ከብዙ ዓመታት በኋላ የመጣው መሐመድና የመሰረተው እስልምና ተመሳሳይ የሃይማኖት መግለጫ (Creed) እንዲኖረው በማሰብ በሱራ ዝ12፡ዝ ላይ “በል አላህ አንድ ነው” ብለው ትርጉም የሰጡትን ሱራ ተከለ። ከዚህ በመነሳትም ሙስሊም ሊቃውንት ተውሒድ የሚባል የሃይማኖት አቋም መግለጫ አመጡ። ዛሬ እንደ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ የምናየው ሙስሊም ወገኖች ስለሚያነሱትና ምን ማለት እንደሆን ስንጠይቃቸው ያለምንም ቁርአናዊ ማስረጃና መሰረት ስለሚያወሩበት ስለ ተውሒድ ካለው ትንሽ ጨልፌ በተከታታይ ክፍላት ላቀርብ ወደድኩ። በማስተዋል እንድናነብ አምላካችን ይርዳን! መልካም ንባብ።

ተውሒድ የሚለው ቃል(ቁርአን ውስጥ በጭራሽ ባይገኝም ቃሉ) ብዙ ጊዜ በሙስሊም ወገኖች ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውልና የሃይማኖታቸው መሰረት ሲሆን አስተምህሮውም አላህ አንድ ብቻ ነው፣ ከሱ ውጪ መመለክ የሚገባው የለም የሚለውን ትርጉም የያዘና አላህ በብቸኝነት ተመላኪ ነው የሚለውን ሃሳብ የሚያስይዝ ነው በማለት ሰፋ ያለ ትንታኔ ይሰጣሉ። ለዚህም ማስረጃ የሚያቀርቡት ሰሩቱ አልኢኽላስ አያ ፩ ላይ ያለውን በል አላህ አንድ ነው የሚል ትርጉም የሰጡትን አያ በመጥቀስ ነው። ይህ ሱራ በእስልምና በጣም ጠቃሚ በመሆኑ የእስልምና እምነት መግለጫ (Creed) በመሆን ሲያገለግል ይህን አያ ደጋግሞ ለሚለውም የተገቡለት የተለያዩ ቃልኪዳኖች ሲኖሩት ደጋግሞ ለሚቀራው ወይም ለሚያነበው የ 50 ዓመት ወይም የ100 ዓመት ሃጢአቱ ይቅር ይባልለታል በማለት ይህንን ሱራ ማንኛውም ሙስሊም ሳይቀራ መዋል እንደሌለበት በመንገር በሙስሊሙ ማህበረሰብ አዕምሮ ውስጥ ይህንን ሱራ በጥቅም ተክለውታል። ይህን ሱራ መረዳትም የእስልምናን ፩/3ኛ መረዳት ማለት ነው ይላሉ ከነቢያቸው መሐመድ የሰሙት የእስልምና መምህራን። ነቢዩ መሐመድም አንዱ ተከታዩ ስለዚህች ሱራ (ሌላኛው ሃዲስ ላይ የመጀመርያዋ አያ) ሲጠይቀው ይህቺ የቁርአን አንድ ሶስትኛ ናት ብሎ መልሶ ነበር(ሱናን ኒሳኢ 995, 996)። ይህ ሁሉ ትርጉምና ቃልኪዳን የተገባለት ይህ ሱራ አሃድ የሚለው ቃል “አንድ” “ነጠላ” “ልዩ” ወዘተ የሚሉ ትርጉሞችን ይዟል በሚል የተረጋገጠ ቁርአናዊ ማስረጃ ባለው ነገር ላይ የተመሰረተ ወይስ ተራ ምኞት? ይህን ጥያቄ መልሱን ለአንባቢ ውሳኔውን የምንተወው ይሆናል። ምናልባትም ሻል ያለ የተማረ ሙስሊም ካገኛችሁም ሌሎችን አያዎች ጠቅሶ ተውሒድን ሊያስረዳችሁ ይሞክራል።

በዚህ “ተውሒድ” ጽንሰ-ሐሳብ ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ቃላት ያሉ ሲሆን አሃድ (أَحَدٌ) እና ዋህድ (وَٰحِدٌ) ይሰኛሉ። እነዚህን ቃላት ሲያብራሯቸውም አንዱና ፍጹሙ፣ ብቸኛውና ልዩው፣ ብቸኛው የሚመስለው የሌለና አቻ የሌለው

በማለት ምንም አይነት ቁርአናዊም ሆነ ሃዲሳዊ መረጃ ሳይሰጡ ይሰብካሉ። አሃድ ማለት ነጠላ የሆነ፣ ብቸኛ የሆነ የሚመስለው የሌለ (unique in his essence) ሲሉት ዋህድ የሚለውን ደሞ በባሕርይውም በአካሉም ነጠላ የሆነ (Singular in his essence and person) ልዩ የሆነ ማለት ነው ይላሉ። ይህን የተውሒድ ጽንሰ-ሃሳብ አንዳንዴ በአራት አንዳንዴ በሶስት የሚከፍሉት ሲሆን ሁሉም ከፍፍል የተንጠለጠለው እነዚህ ሁለት ወሳኝ ቃላት ላይ ነውና እስኪ ቁርአኑን መሰረት አድርገን አሃድ እና ዋህድ ምን ማለት እንደሆኑ እንይ። ማስረጃችንን ከቁርአን ያደረግንበት ምክንያት እነዚህ ቃላት መሰረታዊ ግኝታቸው ከቁርአን ነው ስለተባሉና ተቀጽለው የመጡት በአላህ ማንነትና ምንነት ወይም ባህርይ ዙሪያ በመሆኑ ስለ አላህ ባህርይ ከራሱ ቃል በበለጠ የሚያብራራልን የሚገልጽልን ባለመኖሩ ነው። በመሆኑም መልስ ለመስጠት የሚያስቡ ሙስሊሞችና ኡስታዝ ተብዬዎችም መሰረታዊ መነሻ ከቁርአን በማድረግ እንዲመልሱ እንጂ ነህው አልአረቢያ (የአረብኛ ሰዋስው) በማለት ከቁርአኑ ውጪ ባይጠቅሱና ባይጫዎቱ ስል ማሳሰቢያዬን ከወዲሁ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። ጥያቄችን ስለአላህ ማንነትና ምንነት በመሆኑ የሱ ዘለአለማዊ ንግግር ነው ከተባለው ቁርአን እንጂ ሌላ ሰው ስለአላህ ይሚያስበውን የጻፈውን ነገር መቀበል ይከብዳል። ብታመጡም እስካመናችሁበት ድረስ እንቀበላለን ግን ከአላህ የተሻለ አላህን የሚገልጽው የለምና ቁርአናዊ ማስረጃዎችን አልሆን ካለም ሃዲሳዊ ማስረጃዎችን ብቻ እንድታቀርቡ ስል ወዳጃዊ ማሳሰቢያዬን አስተላልፋለሁ።

<u>እውን አሃድ (أَحَدٌ) ማለት አንድ፣ ነጠላ፣ ብቸኛ፣ ልዩ፣ ወዘተ የሚሏቸውን ሁሉ ትርጉሞች ማለት ነውን?</u>

ይህ ቃል በቁርአኑ ውስጥ ከ31 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሱራቱል ኢኽላስ አያ አንድ ውጪ አንድም ቦታ "ነጠላ፣ አንድ፣ ብቸኛ፣ ልዩ፣ የሚጋራው የሌለ" ወዘተ የሚል አንድም አያ የለም። ይልቁን አሃድ (أَحَدٌ) የሚለው ቃል አንድም No one፣ ማንም Anyone of you፣ ከናንተ መካከል Amongst you ወዘተ የሚሉ ከሚባለው ተቃራኒ የሆነ ትርጉም እንጂ የትኞቹም አያ "አንድ" "ነጠላ" የሚል ትርጉም የለውም። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንይ፥-

የላሚቱ ምዕራፍ አያ 102 (2፡102)

> أُنزِلَ وَمَآ ٱلسِّحْرَ ٱلنَّاسَ يُعَلِّمُونَ كَفَرُواْ ٱلشَّيَٰطِينَ وَلَٰكِنَّ سُلَيْمَٰنُ كَفَرَ وَمَا ۖ سُلَيْمَٰنَ مُلْكِ عَلَىٰ ٱلشَّيَٰطِينُ تَتْلُواْ مَا وَٱتَّبَعُواْ مَا مِنْهُمَا فَيَتَعَلَّمُونَ ۖ تَكْفُرْ فَلَا فِتْنَةٌ نَحْنُ إِنَّمَا يَقُولَآ حَتَّىٰ أَحَدٍ مِنْ يُعَلِّمَانِ وَمَا ۚ وَمَٰرُوتَ هَٰرُوتَ بِبَابِلَ ٱلْمَلَكَيْنِ عَلَى وَلَا يَضُرُّهُمْ مَا وَيَتَعَلَّمُونَ ۚ ٱللَّهِ بِإِذْنِ إِلَّا أَحَدٍ مِنْ بِهِۦ بِضَآرِّينَ هُم وَمَا ۚ وَزَوْجِهِۦ ٱلْمَرْءِ بَيْنَ بِهِۦ يُفَرِّقُونَ كَانُواْ لَوْ ۚ أَنفُسَهُمْ بِهِۦ شَرَوْاْ مَا وَلَبِئْسَ ۚ خَلَٰقٍ مِنْ ٱلْءَاخِرَةِ فِى لَهُۥ مَا ٱشْتَرَىٰهُ لَمَنِ عَلِمُواْ وَلَقَدْ ۚ يَنفَعُهُمْ يَعْلَمُونَ

Pickthall

> And follow that which the devils falsely related against the kingdom of Solomon. Solomon disbelieved not; but the devils disbelieved, teaching mankind magic and that which was revealed to the two angels in Babel, Harut and Marut. Nor did they (the two angels) teach it to anyone till they had said: We are only a temptation, therefore disbelieve not (in the guidance of Allah). And from these two (angles) people learn that by which they cause division between man and wife; but they injure thereby no-one save by Allah's leave. And they learn that which harmeth them and profiteth them not. And surely they do know that he who trafficketh therein will have no (happy) portion in the Hereafter; and surely evil is the price for which they sell their souls, if they but knew.

> ሰይጣናትም በሱለይማን (ሰሎሞን) ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን (ድግምት) ተከተሉ። ሱለይማንም አልካደም፤ (ድግምተኛ አልነበረም)፤ ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲኾኑ ካዱ። ያንንም በባቢል በሁለቱ መላእክት በሃሩትና ማሩት ላይ የተወረደውን ነገር (ያስተምሩዋቸዋል)። «እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም። ከእነሱም በሰውየውና በሚስቱ መካከል በርሱ የሚለዩበትን ነገር ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልኾነ በርሱ አንድንም ጎጂዎች አይደሉም። የሚጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውንም ይማራሉ። የገዛውም ሰው ለርሱ በመጨረሻይቱ አገር ምንም እድል የሌለው መኾኑን በእርግጥ ዐወቁ። ነፍሶቻቸውንም በርሱ የሸጡበት ዋጋ ከፋ! የሚያውቁ በኾኑ ኖሮ (ባልሠሩት ነበር)።

አሃድ የሚለውእዚህ ላይ እንግሊዝኛው No-one ሲለው አማርኛው አንድንም ከሰዎች መካከል (አሃዱ) አንዱንም ነጂዎች አይደሉም ይላል። የሆነን ብቸኛ ልዩ ሰው የሚመለከት ሳይሆን ካለው ጀመሓ ውስጥ አንዱንም ወይንም የትኛውንም ማለት ነው እንደሚታየው።

የላሚቱ ምዕራፍ አያ 285

مِّن أَحَدٍ بَيْنَ نُفَرِّقُ لَا وَرُسُلِهِۦ ۚ وَكُتُبِهِۦ ۚ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ ۚ بِٱللَّهِ ءَامَنَ كُلٌّ ۚ وَٱلْمُؤْمِنُونَ رَّبِّهِۦ ۚ مِن إِلَيْهِ أُنزِلَ بِمَآ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ ٱلْمَصِيرُ وَإِلَيْكَ رَبَّنَا غُفْرَانَكَ ۖ وَأَطَعْنَا سَمِعْنَا وَقَالُوا۟ ۚ رُّسُلِهِۦ ۚ

Pickthall

The messenger believeth in that which hath been revealed unto him from his Lord and (so do) believers. Each one believeth in Allah and His angels and His scriptures and His messengers - We make no distinction between any of His messengers - and they say: We hear, and we obey. (Grant us) Thy forgiveness, our Lord. Unto Thee is the journeying.

መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም።

እንግሊዝኛው Each one ሲለው አማርኛው ደግሞ በአንድም መካከል አንለይም ይላል። ያ ማለትም ከተወረዱትና መጻሕፍትና ከተላኩት ነቢያት ውስጥ አንዱንም አንለይም ማለት ነው።

የኢምራን ቤተሰብ አያ 73 (3፡73)

إِنَّ قُلْ ۗ رَبِّكُمْ عِندَ يُحَآجُّوكُمْ أَوْ أُوتِيتُمْ مَآ مِّثْلَ أَحَدٌ يُؤْتَىٰٓ أَن ٱللَّهِ هُدَى ٱلْهُدَىٰ إِنَّ قُلْ دِينَكُمْ تَبِعَ لِمَن إِلَّا وَلَا تُؤْمِنُوٓا۟ عَلِيمٌ وَٰسِعٌ وَٱللَّهُ ۗ يَشَآءُ مَن يُؤْتِيهِ ٱللَّهِ بِيَدِ ٱلْفَضْلَ

Pickthall

And believe not save in one who followeth your religion - Say (O Muhammad): Lo! the guidance is Allah's Guidance - that anyone is given the like of that which was given unto you or that they may argue with you in the presence of their Lord. Say (O Muhammad): Lo! the bounty is in Allah's hand. He bestoweth it on whom He will. Allah is All-Embracing, All-Knowing.

እናንተ የተሰጣችሁትን ብጤ አንድም ሰው መሰጠቱን ወይም እጌታችሁ ዘንድ የሚከራከሩዋችሁ መኾንን ሃይማኖታችሁን ለተከተለ ሰው ቢኾን እንጂ አትመኑ (አትግለጹ አሉ)። «መምሪያው የአላህ መምሪያ ብቻ ነው» በላቸው። «ችሮታ በአላህ እጅ ነው። ለሚሻው ይሰጠዋል። አላህም ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነው» በላቸው።

እንግሊዝኛው Anyone ሲለው አማርኛው ደግሞ አንድም ሰው መሰጠቱን ይላል። አንባቢ ያስተውል አሃድ የሚለው ቃል ነጠላ ብቸኛ አንድ ብቻ የሚል ትርጉምን አልሰጠም እስካሁን። ይልቁን ከሆነ ቡድን ወይም ተደራሲ መካከል አንደኛውን ሲመለከት ብቻ የሚጠቀምበት ቃል ነው። እንቀጥል ማስረጃዎቹን

የሴቶች ምዕራፍ አያ 43 (4፡43)

وَإِن ۚ تَغْتَسِلُوا۟ حَتَّىٰ سَبِيلٍ عَابِرِى إِلَّا جُنُبًا وَلَا تَقُولُونَ مَا تَعْلَمُوا۟ حَتَّىٰ سُكَٰرَىٰ وَأَنتُمْ ٱلصَّلَوٰةَ تَقْرَبُوا۟ لَا ءَامَنُوا۟ ٱلَّذِينَ يَٰٓأَيُّهَا فَٱمْسَحُوا۟ طَيِّبًا صَعِيدًا فَتَيَمَّمُوا۟ مَآءَ تَجِدُوا۟ فَلَمْ ٱلنِّسَآءَ لَٰمَسْتُمُ أَوْ ٱلْغَآئِطِ مِّنَ مِّنكُم أَحَدٌ جَآءَ أَوْ سَفَرٍ عَلَىٰ أَوْ مَّرْضَىٰٓ كُنتُم غَفُورًا عَفُوًّا كَانَ ٱللَّهَ إِنَّ ۗ وَأَيْدِيكُمْ بِوُجُوهِكُمْ

Pickthall

> O ye who believe! Draw not near unto prayer when ye are drunken, till ye know that which ye utter, nor when ye are polluted, save when journeying upon the road, till ye have bathed. And if ye be ill, or on a journey, or one of you cometh from the closet, or ye have touched women, and ye find not water, then go to high clean soil and rub your faces and your hands (therewith). Lo! Allah is Benign, Forgiving.

> እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም፥ ወይንም ከእናንተ አንዱ ከሳይነምድር ቢመጣ፥ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንጹሕ የኾነን የምድር ገጽ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይ መሓሪ ነውና፡፡

እንግሊዝኛው One-of you ሲለው ከእናንተ አንዱ ከሳይነምድር ቢመጣ ብሎ ቁልጭ ባለ አማርኛ አስቀምጦታል። ካሉት ሙእሚኖች ውስጥ አንዱ ማለት ነው።

የማዕዱ ምዕራፍ አያ 6 (5፡6)

> إِلَى وَأَرْجُلَكُمْ بِرُءُوسِكُمْ وَٱمْسَحُواْ ٱلْمَرَافِقِ إِلَى وَأَيْدِيَكُمْ وُجُوهَكُمْ فَٱغْسِلُواْ ٱلصَّلَوٰةِ إِلَى قُمْتُمْ إِذَا ءَامَنُوٓاْ ٱلَّذِينَ يَٰٓأَيُّهَا لَٰمَسْتُمُ أَوْ ٱلْغَآئِطِ مِّنَ مِّنكُم أَحَدٌ جَآءَ أَوْ سَفَرٍ عَلَىٰ أَوْ مَّرْضَىٰٓ كُنتُم وَإِن ۚ فَٱطَّهَّرُواْ جُنُبًا كُنتُمْ وَإِن ۚ ٱلْكَعْبَيْنِ حَرَجٍ مِّنْ عَلَيْكُم لِيَجْعَلَ ٱللَّهُ يُرِيدُ مَا ۚ مِّنْهُ وَأَيْدِيكُم بِوُجُوهِكُمْ فَٱمْسَحُواْ طَيِّبًا صَعِيدًا فَتَيَمَّمُواْ مَآءً تَجِدُواْ فَلَمْ ٱلنِّسَآءَ تَشْكُرُونَ لَعَلَّكُمْ عَلَيْكُمْ نِعْمَتَهُۥ وَلِيُتِمَّ لِيُطَهِّرَكُمْ يُرِيدُ وَلَٰكِن

Pickthall

> O ye who believe! When ye rise up for prayer, wash you faces, and your hands up to the elbows, and lightly rub your heads and (wash) your feet up to the ankles. And if ye are unclean, purify yourselves. And if ye are sick or on a journey, or one of you cometh from the closet, or ye have had contact with women, and ye find not water, then go to clean, high ground and rub your faces and your hands with some of it. Allah would not place a burden on you, but He would purify you and would perfect His grace upon you, that ye may give thanks.

> እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፡፡ (ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት «ጀናባ») ብትኾኑ (ገላችሁን) ታጠቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም ወይም ከእናንተ አንዳችሁ ከሳይነ ምድር ቢመጣ ወይም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ ንጹሕን የምድር ገጽ አስቡ ፡፡ ከሱም ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን አብሱ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ምንም ችግር ሊያደርግ አይሻም፡፡ ግን ታመሰግኑ ዘንድ ሊያጠራችሁና ጸጋውን በእናንተ ላይ ሊሞላ ይሻል፡፡

ይሄም ልክ እንደላይኛው ቃል በቃል ከናንተ አንዱ ብሎ ተርጉሞታል።

የንስሐ ምዕራፍ አያ 6 (9፡6)

بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَّا يَعْلَمُونَ ذَٰلِكَ ۚ مَأْمَنَهُ ۚ أَبْلِغْهُ ثُمَّ ٱللَّهِ كَلَٰمَ يَسْمَعَ حَتَّىٰ فَأَجِرْهُ ٱسْتَجَارَكَ ٱلْمُشْرِكِينَ مِّنَ وَإِنْ أَحَدٌ

Pickthall

And if anyone of the idolaters seeketh thy protection (O Muhammad), then protect him so that he may hear the Word of Allah, and afterward convey him to his place of safety. That is because they are a folk who know not.

ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፡፡ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፡፡ ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው፡፡

አሃዱ ሚን ሙሽሪኩን ከአጋሪዎቹ (አሃዱ) አንዱ ተብሎ ተተርጉሟል እንግሊዝኛውም Anyone ብሎታል።

የፈጣሪዋ ምዕራፍ አያ 41 እና 42 ተመሳሳይ ሃሳብ ስላላቸው አንዱን እንጥቀስ (35፡41 እና 42)

إِنَّهُ كَانَ حَلِيمًا غَفُورًا ۚ بَعْدِهِۦ ۚ مِّنْ أَحَدٍ مِنْ أَمْسَكَهُمَا إِنْ زَالَتَآ وَلَئِن ۚ تَزُولَا أَن وَٱلْأَرْضَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ يُمْسِكُ إِنَّ ٱللَّهَ

Pickthall

Lo! Allah graspeth the heavens and the earth that they deviate not, and if they were to deviate there is not one that could grasp them after Him. Lo! He is ever Clement, Forgiving.

አላህ ሰማያትንና ምድርን እንዳይወገዱ ይይዛቸዋል፡፡ ቢወገዱም ከእርሱ ሌላ አንድም የሚይዛቸው የለም፡፡ እነሆ እርሱ ታጋሽ መሓሪ ነውና፡፡

እዚህ ላይም አንድም የተባለ ሲሆን የሚያሳየውም ከፍጥረት መካከል አላህ የያዘውን መያዝ የሚችል አንድም ፍጥረት አለመኖሩን ነው።

የመርየም ምዕራፍ አያ 98 (19፡98)

رِكْزًا لَهُمْ تَسْمَعُ أَوْ أَحَدٍ مِّنْ مِنْهُم تُحِسُّ هَلْ قَرْنٍ مِّن قَبْلَهُم أَهْلَكْنَا وَكَمْ

Pickthall

And how many a generation before them have we destroyed! Canst thou (Muhammad) see a single man of them, or hear from them the slightest sound?

ከእነሱም በፊት ከክፍለ ዘመናት ሕዝቦች ብዙዎችን አጥፍተናል፡፡ ከእነሱ አንድን እንኳ ታያለህን? ወይስ ለእነሱ ሹክሹክታን ትሰማለህን?

እዚህም ላይ ከሰዎቹ መካከል አንድን እንኳን ታያለህን ብሎ ከበዙዎች ማንም አለመኖሩን ያሳያል።

የአረጋጋጪቱ ምዕራፍ አያ 47 (69:47)

حَٰجِزِينَ عَنْهُ أَحَدٍ مِّنْ مِنكُم فَمَا

Pickthall

And not one of you could have held Us off from him.

ከእናንተም ውስጥ ከእርሱ ላይ ከልካዮች ምንም አይኖሩም::

Not one of you ሲለው አማርኛውም ተባብሮ ከእናንተ ውስጥ ብሎታል።

ማስረጃውን ያበዛሁት ካነሰ ውሸት ነው ለማለት እንዳይመቻቸው ነው እንጂ ማስረጃ በመደርደር ለማሰልቸት አይደለም። አንዲት አያም በቂ ነበረች ግን ማለቃቀሻ እንዳያገኙ በማሰብ ነው።

እስካሁን እንዳየነው አሃድ ማለት የሆነ ቡድን ወይም ተደራሲ ውስጥ ያለ አንድ አካልን ነጥሎ አውጥቶ ማውራት ወይም መድረስ ሲፈለግ የሚውል ቃል መሆኑን ከቁርአኑ ከራሱ ከአላህ ቃል አይተናል። ከአሊሞቹ ወይም ከተፍሲር ወይም ከሃዲስ አይደለም ከራሱ ከባለቤቱ እንጂ። ታዲያ እንዲህ ከሆነ ኢኽላስ አያ 1 ላይ ያለው "በል አላህ አንድ ነው" ሳይሆን "በል አላህ አንዱ ነው" የሚለው ትክክለኛ ትርጉሙ ሆኖ እናገኘዋለን። ነገርግን ሙስሊም አሊሞች "አንዱ" ብለው ያልተረጎሙት አንዱ ምን? ከምን መካከል ነው አንዱ? የሚመስለው ስላለ ነው አንዱ የተባለው? የሚሉ ጥያቄዎችን ስለሚያነርፍ ከዚህ ሁሉ መገላገያ መንገዱ አንድ ነው አንድ ነው በቃ ብሎ ሰዉ የቃሉን ትርጉም ጠለቅ ብሎ እንዳይመረምርና እንዳይፈትሽ ደጋግሞ መንገርና እውነት ነው ብለው እስኪቀበሉ ድረስ የሱራውን ጥቅም ማስረጽ ነው። እንደዚህ ከሆነ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ይህንን ሱራ በማለቱ የሚያገኘውን ጥቅም እንጂ ምን ማለት እንደሆነ አይመራመርም እጅግ በጣም በተደጋጋሚም አንድ ነው አንድ ነው አንድ ነው እያሉ በማስደገም ከተጠያቂነት ያድኑታል ሱራውን። አሁን ግን እንደዛ በማድረግ መዳን የሚቻል አይመስልም። ትውልዱ አዕምሮውን ይጠቀማል አሊሞቹ የማያገኙትን መኖሩንም እንኳን የማያውቁትን መጽሐፍ ከቤቱ ቁጭ ብሎ ሳይለፋ ሳይወጣ ሳይወርድ ያገኛል በቋንቋ እንዳይደበቁ አረብኛ ስለማትችል እንዳይሉም ዘመኑ ለውሸት አልመች አለ።

አሃድ (أَحَدٌ) የሚለው ቃል ትርጉም በቁርአኑ ሙሉ ይሄ ሆኖ ሳለ አላሁ አሃድ በምን ሂሳብ ነጠላ አንድ ሆነ? ብለን መጠየቅ የግድ ይሆንብናል። ሙስሊም መምህራንም ቁርአኑን መሰረት በማድረግ ቃሉ ነጠላ ማንነትን ለመግለጽ እዚህ እዚህ ላይ ውሏል በዛ መሰረትነት ላይ ነው ኢኽላስ ላይ ነጠላ አንድ የሚል ትርጉም የሰጠው ብላችሁ መልስ ልትሰጡ ይገባል። ተፍሲር ማውዱዲ እንኳን 112:2 ላይ አላሁ ሰመድ የሚለውን ሲፈስር ይህን "አሃድ" የሚለውን ቃል "It is used in an indefinite sense" ማለትም ባለቤቱ አላህ ቢሆንም አሃዱ መባሉን indefinite ማለቱን ልብ ይሏል ምክንያቱም አንዱ ምን? ሲባል መልስ ስለሌለው መሆኑንና ያላለቀ አረፍተነገር በመሆኑ Indefinite sense ማለቱም ለዚህ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ቁርአኑን መሰረት በማድረግ የእስልምና ምሁራን መመለስ አለባቸው የምለው ለተራው አማኝ አይደለም ለራሳቸው እንኳን መግባቱን እርግጠኛ መሆን በማይቻልበት የሰዋስው ረዢም ረብ የለሽ ማብራሪያ ስለሚሰጡና ጥያቄውን የማይመልስ ምላሽ ስለሚሱጡና ረዢም ኢ-ቁርአናዊ ማስረጃ ተብዬ ስለሚያንዘባዝቡ ነው። ከዛ ይልቅ ቁርአኑ ውስጥ አሃድ የሚለው ቃል ነጠላ ማንነትን ለመግለጽ በዚህ በዚህ ውሏል በዚህም ምክንያት አላሁ አሃድ ሲባል አንድ ነው ተብሎ የተተረጎመው በዚህ በዚህ ምክንያት ነው ብሎ ማስረዳት ያስፈልጋል።

አሃድ የሚለው ቃል አሃደን፣ አሃዱን፣ አሃድ፣ አሃዲን ወዘተ በሚል ሲመጣ አነባበብ እንጂ ትርጉም አይቀይርምና ተረጋግተን እናንብብ እናስትውል። የአቀራር ዘዴን ከትርጉም ጋር የምታያይዙ ሙስሊሞችን ስላጋጠመኝ ነው ቃሉ በተለያየ ባለቤት አመልካች ቢመጣም ትርጉሙን አይለቅም የምለው። እሺ አሃድ የሚለውን ይህን ያክል ካየን ዘንድ በቀጣይ ክፍል ደሞ (Unique in his essence) የሚመስለው የሌለ፣ ብቸኛ፣ ማንም ማን የማይመስለው ወዘተርፈ የሚል ትርጉም ይሰጣል ያሉትን ዋህድ የሚለውን ቃል እንመልከታለን። ቸር እንሰንብት! ደካማ ወንድማችሁን በጸሎታችሁ አስቡኝ!